# ለተራበው ዳቦ ወይስ ስለ ዳቦ ወሬ?

ከ ፅጌ ዋስይሁን

ከራስ ዳሽን ተራራ ስር ቆመው የፎገራ ሜዳ ታየን የሚሉ ጥቂቶች አይደሉም። ያ አረመኔ ኮሎኔል መንግስቱ ስንት ሺ ሕዝብ በግፍ ጨርሶና ስንቱን ገላ በስየል ጠብሶ ዝንብ እንኳን መግደል አልወድም ሲል ተደምጧል። የዘረኛ አምባገነንነትን ያሰፈነው መለስ ዜናዊም ዴሞክራሲን መሰረትኩ ብሎ ከመመፃደቁ ሌላ በሀገሪቷ የገባው ረሀብ ከ 14 ሚሊዮን ያላነሰ ሕዝብን እያሰቃየ ባለበት ድርቅ እንጂ ረሀብ የለም ብሎ በድፍረት ክዷል። ዋሾና ወሮበላ ሚስቱም ልጄን የግል ትምህርት ቤት ለመላክ ገንዘብ ይቸግረኛል ስትል አሰልጣኟ ባሏም ከመፅሀፎቼ ሌላ ንብረት የለኝም ብሎ፤ እመኑኝ ብሎ ጥቂት ጊዜ በፊት ተማፅኖናል። የአራዳ ልጆች ሞኝህን ብላ ይሉታል ። ለወያኔ ገና ስልጣን ሳይደርስ ጀምሮ ሲያገለግሉ የታዘብናቸው ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሐቅም በእሳቸው ብሶ የሀገር ምሁሮችን በገናና አዲስ ዓመት መልዕክታቸው ሊወቅሱ ሲሞክሩ አድህነነ ከመዓቱ ከቅሌቱ ሰውረነ ማለት ተገደናል፡ የወያኔ አገዛዝ በዋሾዎች የተሞላ ለመሆኑ ተጠራጣሪ ዜጋ ብዙ አይደለም። ቢሆንም አውቀ የተኛ ወይም ነጋ ጠባ የሚጃጃል ደግሞ አይጠፉምና ነቃ እንበል መልዕክቶች ወቅታዊነት አላቸው።

በመሆኑም በቅሎ አባትሽ ማን ሲሏት እናቴ ፈረስ ናት ዓይነት ንግግር በወያኔዎች ይወደዳል። ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ ። ለተራበው ዳቦ ወይስ ስለ ዳቦ ወሬ ለሚለው የወያኔ መልሱ ስለ ዳቦ ወሬ መሆኑ የሚታወቅ ነው። ይባስ ብሎ የወያኔው ቁንጮ ረሀብ የለም በሀገሩ ብሎ 14 ሚሊዮን ሰው ለሞት መዳረጉ ለኔ ጉዳዬ አይደለም ብሏል። ይህ ምሳሌ ሆኖ የሚያሳየንና የሚሰጠን ትምህርት በወግ ጥረቃ ሳንታለል ና የትኩረት ነጥቦችን ሳንስት መታገል እንዳለብን ነው። ወያኔ ቀደም ሲል የሀሰት ዜና ስራዬ ብለው የሚያሰራጩ ቅጥረኞቹን 03 በሚለው ተቋም ስር ሰብስቦ አሰማርቶ ነበር። አደናጋሪና ዜናዎችንና ከፋፋይ አሉባልታዎችን የሚያሰራጩ ናቸው። ከዘመኑ ጋር አብሮ ለመሄድም በወያኔ  ቁጥጥር ስር ያሉ ራዲዮኖችና ድረ ገፆችም በርክተዋል። የእነዚህም ሁሉ ዋናው ተልዕኮ  ስለ ወያኔ አገዛዝ የተንሸዋረረና ለወያኔ የሚያመች ዜናን ማቅረብ፤ በተቃዋሚዎች ላይ የሀሰት ዜናዎችና ክሶችን ማሰራጨት፤ ሕዝብን በብሄረሰብና በሀይማኖት መከፋፈል፤ ማለትም ነጋ ጠባ  የውሸት ከበሮን መደለቅ ማለት ነው። የነዚህ  የወያኔ መሳሪያዎች መሰሪ ተልዕኮ ደግሞ ዋናውን ጉዳይ በአልባሌና ንዑስ ጉዳዮች እንደ ጭጋግ መሸፋፈን ነው። ለዚህምብዙዎች ሰለባ ሆነው በፍርፋሪው ሲጣሉ ወያኔ ዳቦውን ወደ ቤቱ ያስገባል። ለምሳሌ ከ1997 ኡ የምርጫ ሂደትና ከተከተለው ፍጅትና አፈና አንፃር ዋናው ጉዳይ የወያኔ ቡድን የሕዝብን ድምፅ በሀይልና በአፈና መስረቁ ሆኖ ሳለ ሌሎች መሰረታዊ ያልሆኑ ነጥቦች ላይ ዋናው ግብግብ ያተኩር ዘንድ ወያኔ በስልት መጠምዘዙ የሚታወስ ነው። የፖለቲካ እስረኞችም ጉዳይ ቢሆን 35 ሺ ዜጋ ታስሮ ባለበት መቶ ሀያው መሪዎች ይፈቱ በሚለው ብቻ እንዲጮህና ቀጥሎም በድርጅት ወይ ግለሰብ እስረኞች ላይ ብቻ እንዲተኮር በማድረግም የልቡን አድርሷል፤ ዋናውን የወያኔን ህገወጥ አገዛዝ ማክተም ጥያቄ ወደ ጎን አስደርጓል። በድርጅቶች መሀልም

የርስ በርስ ጠብና ውንጀላን አራግቦ እፎይ ብሏል፡፡ ይህን ስልት የተማሩትም ለወያኔ አገዛዝ በገቢ ርና በገሀድ እየጠቀሙ አሉ የሚባሉት አስታራቂ ተብዬ ሽማግለዎችም በአስቸኳይሌሎችንም እናስፈታለን ብለው የተናገሩት ያው ሳይውል ሳያድር ማደናገሪያ መሆኑ ተጋልጧል፡፡ ለምሳሌ አንድም ኢሕአፓ የተባለና ለዓመታት ታግቶ የቆየ እስረኛ ሲፈታ አልታየም፡፡

በአሁኑ ጊዜ ወያኔ የወረወረው ሌላ የማደናገሪያ አጥንት ዙሪያ ብዙ ጫጫታና ጩኸት ይሰማል፡፡ ይኸውም መለስ ዜናዊና የህጋዊ ድርጅቶች መሪዎች ተፈራረሙት የተባለውን የስነ ስርዓት ህግ ይመለከታል፡፡ ድራማው ወይ ተወኔቱ ለብ እንዲል ደግሞ መድረክ በሚለው ሰር የተሰባሰቡ ና በአውነትም ተቃዋሚ መሆናቸውን ለሕዝብ ማሳመን ያቃታቸው ቡድኖች ደግሞ በስምምነቱ የለንበትም ብለው ሲያንገራገሩ ተደምጠዋል፡፡ የዚህ ፊርማ ዜናነት በእውነቱ አስገራሚነቱ ውሻ ሰው ነከሰ የሚለውን ዜና ያህል ነው፡፡ በመሰረቱ ወያኔ ምርጫ ብሎ የሚጮኸውን በተመለከተ ዋናው ጉዳይ በወያኔ አገዛዝ ስር ነፃና ፍትህዊ መርጫ መካሄድ አለመቻሉን የሚመለከት ነው፡፡ ቁም ነገሩ በ1997ኡ ተመክሮ እንደታየው ሁሉ የምርጫው ህግና ኮሚሽን የወያኔ እስከሆኑ ድረስ ፍትሃዊ ምርጫ ሊኖር አለመቻሉ ነው፡፡ ቁም ነገሩ በዚህ የወያኔ አጓጉል ጨዋታ ገብቶ ከመራገጥና ማላገጫ ያ ከመሆን ይልቅ በምርጫው አለመሳተፍ የሚል ነው፡፡ ወያኔ በምርጫው ላይ ማዕቀብ የሚለው ዋና ርዕስ እንዳይሆን የራሱን ሴራ ሸረበ ፡፡ የምርጫ ስነ ስርዓት ላይ ውይይት ብሎ በማስጀመር-- ይህ ህገ ወጥ ቡድን የፈረመውን ሰነድ ቀለሙ ሳይደርቅ ቀዶ መጣል ልምዱ ያልሆነ ይመስል-- በዚህ ዙሪያ ትኩረት እንዲደረግ ለፈፈ ፡፡ ስምምነት ተደረሰ በሚባልበት ጊዜም በስልት ፈራሚዎችን በተለይም የመኢአድን መሪ በአወዛጋቢ ፎቶዎች አማካ ኝነት ይፋ በማውጣት ይህ እንዴት ይደረጋል የሚለውን ክርክር ራሱም አራገበ ፡፡ ይህ ሁኔታ ያበሳጫቸው ለሁኔታው ምላሽ ሲሰጡና ጭቅጭቁ ሲደራም ዋናው ርዕስ--በስነ ስርዓት ጉዳይ ስምምነት ተደረሰ አልተደረሰ ዋናው ጉዳይ ማለትም ምንም ቢሆን ምን በወያኔ ስር ፍትሃዊ ምርጫ አይቻልምና ማዕቀብ ይደረግ የሚለው አማራጭና ትኩረት-- ተደብሰበሰ ፡፡ መለስና በረከት አምርረው ከሚጠሏቸው የመኢአድ መሪ ጋር ፎቶ መነሳትና መጨባበጥ ግቡ ምን መሆኑ ን መረዳት የተሳናቸው ክፍሎች (ምናልባትም ፎቶ የተነሱትም ጭምር) ከወያኔ ተንኮል ከመጋረ ጃው በስተጀርባ ያለውን ተገንዝበው ትኩረታቸውን ማስተካከል አልቻሉም፡፡

የውዝግቡን ይዘት ስንቃኝ ህጋዊ የተባሉት ድርጅቶች የወያኔን ህገ መንግስት ተብዬ ሰነድ ቀደም ብለው የተቀበሉና በዚሁም መሰረት ያለውን አገዛዝ በጠላትነት ያልፈረጁ ናቸው፡፡ ሁሉም እንኳን ተፎካካሪ እንጂ ተቃዋሚ አይደለንም ብለው ባይምሉም በምርጫው ላይ ማዕቀብ ማድረገን መምረጥ እስካቃታቸው ድረስ የፓርላማ ወንበሮችን በተቻለ ለማሸነፍ ያዋጣናል የሚሉ ትን መንገድ መከተልና መለሳለሱ የሚጠበቅባቸው ነው፡፡ በአንፃሩ በሌላ መንገድ የሚታገሉትን ድርጅቶች መወንጀልና ለወያኔ የገደል ማሚቴ መሆን አይገባቸውም ቢባል ትክክል ነው፡፡ ስለዚ ህም በአሁኑ ጊዜ የመኢአድ መሪ ከመለስ ዜናዊና በረከት ጋር ተጨባበጡ ተስማሙ በእውነቱ

ብዙ ጊዜ ሊጠፋበት የሚገባ ጉዳይ አይደለም። በ1997ም ቢሆን የምርጫው ህግና ኮሚሽን ሳይለ ወጡ በምርጫው እንገባለን ብለው የገቡ ነበሩ። ከዚህ ተመክሮ የተማሩት ትምህርት ከሌለ ለዚሁ ተጠያቂ ራሳቸው ናቸው--ነግ ተጎጂም። ስለሆነም ሀገር ወዳዱ አተኩሮ መገኘት ያለበት በወያኔ ምርጫ ላይ ሕዝብ ማዕቀብ እንዲያደርግ መቀስቀስ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃም የወያኔ የምርጫ ሂደት ሙሉ በሙሉ የተጭበረበረ መሆኑንና እንደሚሆን ማጋለጥና የወያኔን አገዛዝ ለመጣል መደረግ ያለበትን ትግል ማፋፋምና ማጠናከር ነው። ይህ ተዘንግቶ በጉንጭ አልፋ ንትርክ ላይ ካተኮረ አትራፊው መዘዘኛው የወያኔ አገዛዝ ብቻ ይሆናል።

ተደጋግሞ እንደተነገረው ሕዝብም ሰባራ የትም የማይሄድ ባቡር ወይም አውቶቡስን መሳፈር እንደሌለበት ማወቅ አለበት፤፤ ባቡሩና አውቶቡስ ምን ቢያጋጊጡና ማራኪ ሙዚቃን ቢያሰሙ ሰባራ ከሆኑ የትም አይሄዱም፤ ከቆሙበት ፈቅ አይሉም። አያንጉዙም። ድርጅቶችም ሰባራ ባቡር ከሆኑ ማለትም የሕዝብን ግብ የማያደርሱ የማያሟሉ ከሆኑ ጠቀሜታ የላቸውም። መሪዎች ነን ያሉትም ትግል ሳይጀምሩ ወገቤን የሚሉ ከሆኑ ፋይዳ አይኖራቸውም። ፋኖ ነን ያሉትም በፋኖነ ት መሰማራት እንጂ ስለ ፋኖነት በማውራት መቆም የለባቸውም። ጉዳዩ የሕዝብን ና የሀገርን መሰረታዊ ጥቅምና ህልውና የሚመለከት በመሆኑ በይሉኝታና በአትንኳቸው አትተቿቸው የሚታለፍ ሊሆን አይገባውም። ስለ ዳቦ ወይም ስለ ትግል ወሬው አብቅቶ ትግሉ መጀመር አለበ ት፤ የተራበውም ዳቦ ወይም እንጀራን ማግኘት አለበት ማለት ነው። ይህን ተገንዝበን ትግሉን በርቱዕና ቀጥተኛ ወይም ፍሬያማ መስመር ማስኬድ የምንችለው ወያኔ አቅጣጫ ሊያስተን በቅጥ ረኞቹ አማካይነት ሲጥር እምቢ አንሰማህም አንከተልህም በማለት ብቻ ነው። በቅጥረኞቹ ማለትም በወያኔ ራዲዮኖች፤ ጋዜጦችና ድረ ገፆች ላይ ማዕቀብ ማድረግ ያስፈልጋል። ትኩረታች ንን በፀረ ወያኔው ትግል ላይ በማድረግና ዋናውን ጠላት ከሌላው በመለየት፤ መለስተኛ ቅራኔዎች ን ዋና ባለማድረግ፤ በሕዝብ ጎራ አጓጉል መካረር እንዳይኖር በመጣር፤ የወያኔ ሰርጎ ገቦች ሆነው በሽፋን ግን ፀረ ወያኔ ነን እያሉ ሕዝብን የሚከፋፍሉትን በማጋለጥና በመነጠል መታገል መቻል አለብን። ፀረ ወያኔ ነኝ የሚለው ሁሉ በሀቅ ፀረ ወያኔ ነው ማለት አይደለምና ተግባሩና ተጨባጭ አቅዋሙ መመርመርና መጠናት አለበት።ድርጅቶችም ለሕዝብና ለሀገር ቆምን እስካሉ ድረስ በሕዝብ ሲተቹ ትሁት አድማጭ ሆነው መገኘት ይገባቸዋል። አፍራሹን ከተቆርቋሪ መለየት መቻል ያስፈልጋል። በአሁኑ ጊዜ በሰበብ አስባቡ አንዴ ከግራ አንዴ ከቀኝ፤ ለድርቁም ለጎርፉም በኢሕአፓ ላይ ክስና ዘለፋን የሚያዘንቡ ክፍሎች ወደዱም ጠሉም ለፀረ ኢሕአፓው ወያኔ ጠቃሚ አገልጋይ መሆናቸውን ማወቅ ይገባል። ሁሉም ድርጅት ለራሱ ስህተት ራሱ ተጠያቂ መሆን አለበት፤ በወያኔም ከተወናበደ ጥፋቱን ማመን ይኖርበታል። የሆነ ድርጅት ፍልስልሱ ከወጣ ዶማውን ኢሕአፓ እጅ ለማስገባት መፍጨርጨሩ የሚያዋጣ አይሆንም--ለመፍረሱ ተጠያ ቂ ራሱ ድርጅቱ ነውና። ወያኔም ቢሆን ተቃዋሚዎቹንና ጠላቶቹን ማፍረስ ግዴታውና ተልኮው ነውና ለምን አፈረሰን ብሎ ማልቀሱ አዛኝ አያተርፍም። መጠንቀቅና ራስን መጠበቅ መቅደም ነበረበትና። በመሆኑም ዛሬ የትግላችን ትኩረት አይዛባ ስንል መልዕክቱ ለወያኔ ተንኮል ሰለባ መሆናችን ይቁም፤ ለወያኔ ወሬ አናፋሾች ጆሮ አንስጥ፤ እናጋልጣቸው ማዕቀብ እናድርግባቸው

ለማለት ነው፡፡ አልፎም ዛሬ ዋናው ትኩረታችን  የወያኔ አገዛዝ ይውደም የሚልና ይህንንም እውን ማድረጊያ ትግል ላይ መሆን አለበት ለማለት ነው፡፡  የወያኔን ምርጫ በተመለከተም ሰነድ ተፈረመ አልተፈረመ ትኩረታችን ሊስብ የሚችል ሂደት መሆን የለበትም፡፡ ማተኮር ያለብን በምርጫው ላይ ማዕቀብ አድርጉ ጥሪና ቅስቀሳ ላይና አልፎም በወያኔ ስር ምንም ፍትሃዊ ምርጫ ሊደረግ እንደማይችል ለዓለም ህብረተሰብ (የታወቀ ቢሆንም) ማስረዳቱ ላይ መሆን አለበት፡፡ በወያኔ ፓርላማ ማን ምን ያህል ወንበር አገኘ ወይም ሊያገኝ ይችላል ጥያቄ የሕዝብን ትኩረት የሚስብና የሚሰርቅ ወይም እንቅልፍ ሊነሳ የሚችል ጉዳይ አይደለም--ሁሉም ወንበር ወያኔ ወያኔን የሚሸት በንፁሕን ደም የታጠበ ነውና፡፡ የሚቀመጥበት ሁሉ ይቆሸሻልናም ነው፡፡ ዛሬም ቢሆን ነገ ግንቦት ወያኔ የምርጫው ዋና አሸናፊ መሆኑ የታወቀ ነውና ፡፡  የፖለቲካ እስረኛ ጉዳይን በተመለከተም በወያኔ ስር ፍትህ ተገኝቶ ሁሉም ይፈታሉ ባንልም፤ ሁሉም ይፈቱ ጩኸ ታችን ግን መቆም ያለበት አይደለም፡፡ ሁሉም የሚለውንም በግለሰብ መተካቱ የወያኔን ጨዋታ ማስተጋባት መሆኑም መታወቅ አለበት፡፡

ዴሞክራሲን እንጂ ስለ ዴሞክራሲ ወሬን አንፈልግም፡፡ የወያኔን መወገድ እንጂ ከወያኔ ጋር መተቃቀፍን አንፈልግም--አውሬ ቢጨምቱለት ሊያዝን!  የሕዝብ ያልሆነ ምርጫ የሚያደርጉ ለዚሁ በሕዝብ መጠየቃቸው አይቀርምና በበኩላችን ትግላችን ወያኔን በማስወገዱ ላይ ያተኩር እንላለን፡፡